## እያለፈ ነው ዘመኔ

እያለፈ ነው ዘመኔ ትዕዛዙን ሳለፈፅም ወየው ለኔ(2)
በጠራኝ ጊዜ ምን እላለሁ ና ብሎ ወደ እኔ(2)

በወጣትነቴ ሳልሠራ እያየሁ አለፈኝ ብዙ አዝመራ(2)
ከእንግዲህ በመስራት ጌታ ሆይ ልኑር ከአንተ ጋራ(2)

የማስብበት በየዕለቱ ንጹሕ ልብ ስጠኝ አቤቱ(2)
ከትዕዛዝህ ውጭ በመሆን እንዳልኖር በከንቱ(2)

እንደየሥራው ለመክፈል በግርማ መንግሥቱ ሲመጣ(2)
ማን ይሆን የሚቆም ከፊቱ ፈተናን የወጣ(2)

እንዳያስቷችሁ ተጠንቀቁ እየተማራችሁ ከቃሉ(2)
ይመጣሉና በእርሱ ስም አምላክ ነን የሚሉ(2)

ትዕግሥትን በመያዝ ሁላችሁ እስከ መጨረሻው ጠንክሩ(2)
ያን ጊዜ ይሆናል በእርሱ ዘንድ የማዳን ተግባሩ(2)

## እኔስ በምግባሬ ደካማ ሆኛለሁ

እኔስ በምግባሬ ደካማ ሆኛለሁ
እዘኚልኝ ድንግል እለምንሻለሁ(2)

ያንን የእሳት ባህር እንዳላይ አደራ
ድረሺልኝ ድንግል ስምሽን ስጠራ(2)

አዝ

የዳዊት መሰንቆ የኤልያስ መና
የናሆም መድኃኒት ንኢ በደመና(2)

አዝ

አንቺ ነሽ ጉልበቴ በደከመኝ ጊዜ
የልቤ መጽናኛ እረዳት ምርኩዜ(2)

አዝ

አፈሳለሁ እንባ በጣም ተጨንቄ
እማፀንሻለሁ በደሌን አውቄ(2)